የአበራ ለማ የዲቪዲ ግጥሞች

በዓለማየሁ ታዬ

alalemayehu@yhoo.com

አበራ ለማ ነባር በለቅኔ፥ ደራሲ፥ ጋዜጠኛና ሃያሲ ነው። ‘ኩል ወይስ ጥላሸት”፥ “የማለዳ ስንቅ” ፥ “አውጫጭኝ” ፥ “ ሽበት” ፥“ መቆያ” ፥ “ሕይወትና ሞት”፥ የማለዳ ስንቅ፥ ሞገደኛው ነውጤ ወዘተ... በተሰኙ መጻሕፍቱ የምናውቀው ደራሲ፤ “እውነትም እኛ...” በሚል ርእስ አዲስ የግጥም ቪዲዮ መድበል በዲቪዲ ይዞልን ቀርቧል። 25 ግጥሞች የተካተቱበት ይህ መድበል ምስልና ድምጽ ተቀናብረው የቀረቡበት የዘመኑ ቴክኖሎጂ ውጤት ነው። በዲቪዲው ላይ ከቀረቡት ግጥሞች መካከል በጥቂቶቹ ላይ የተሞከረውን ኪናዊ ምልከታ እነሆ!

ባለቅኔው ከበደ ሚካኤል

ፈልቀሽ የተገኘሽ ከሹበርት ራስ

ከቤቶቨን ናላ ከሞዛርት መንፈስ

ከሾፐን ትካዜ ከያሬድ ልቦና

መዐዛ የሞላብሽ የብስጭት ቃና

ረቂቋ ድምጽ ሆይ ውቢቷ ሙዚቃ

ንጽህት እንደ ፀሃይ ውብ እንደ ጨረቃ

ብሎ ያወደሳትን ሙዚቃ አበራ ለማ “እሱንአኑሩልኝ” በሚል ርእስ እንደሚከተለው ዘምሯታል።

የግጥሙ ሰራዊት አዝማች ....

መሰንቆን ጥሩልኝ - ክራርን አምጡልኝ

ዋሽንትን ተዉልኝ - እሱን አኑሩልኝ

እሩቅ ነው - መንገዱ

እርብትብት ነው - ሆዱ

ብዙ ነው - ትውልዱ

ጥቂት ነው - ዘመዱ

እሱን አኑሩልኝ “መወድስ” ቅኔ ናት። መወድሱ የቀረበው ለባህል የሙዚቃ መሳሪያዎቻችን ለመሰንቆ፥ ለክራርና ለዋሽንት ነው።

የግጥሙ ሰራዊት አዝማች በሙላት ሶስት ግዜ ተሰናኝቶል። በዚህ ግጥም መወድስ የቀረበላቸው የሙዚቃ መሳሪያዎችም እያንዳንዳቸው አንድ አንድ አንጓ ተሰይሞላቸው በሶስት አንጓ ይደመጣሉ። ይህ በሶስት ምድብ የመከፋፈል ዘዬ የግጥሙን ዜማ፤ ምትና ምጣኔ አስተካክሎታል፤ አሳምሮታል። ግጥምን ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘሮች የሚለየው ለይዘት ብቻ ሳይሆን ለቅርጽም መጠበቡ ነው። ይህ ቅርጻዊ ተመጣጥኖ balance እና ውህደት harmony ታዲያ ሲነበብ፤ ለኢይን ሲደመጥ ፤ ለጆሮ የተስተካከለና የሚጣፍጥ

t.me/BooksandYou

ምስል ወ ድምጽ መከሰቱ እንዲሁ በአጋጣሚ የመጣ ሳይሆን፤ ገጣሚው ለዜማ ካለው ስሱነት SENSITIVITY የተወለደ መሆኑን ልብ ይሏል። ምሁራን እንደሚሉትም…

‘Poetry which has been defined as the harmonious unison of man with nature, poetry therefore, will be called musical thought. The poet is he who thinks in that manner.” Carlyle

የመሰንቆው ጭራ - ያ ጥምር ያ ድምር

እራሱን ዘንግቶ - ሌላን የሚያዘክር

ተናግሮ አናግሮ

ውስጠትን ኮርኩሮ….

የመሰንቆው ጭራ በሰውኛ ዘይቤ እንደ ቅን ጎልማሳ የራሱን ነገር ቸል ብሎ ሌሎችን የሚያዘክር፤ ውስጠትን በስውር ጣቶቹ የሚኮረኩር የእምባ ቋትን የሚፈታና ግምባርን በቁጣ የሚያኮሳትር ተናግሮ የሚያናግር ሆኖ በገጣሚው እይታ ተስሎል።

እነ ክራርና ዋሽንትም እንደየብጤታቸውና እንደየባህሪያቸው ተወድሰዋል።

“ክራር ነኝ!…” ይለኛል - ደም ሥሩን አክርሮ

ስሜቴን ለማክረር - ረቂቅ ኪኑን ጭሮ….

ሕይወቴን ሊያወጋኝ - ሕይወቱን አውግቶ

“ያዝ አርገኝ!…” ይለኛል - ሌሊቱን አንግቶ

ሽሜን አጎፍሮ - ጉብል አሸብቶ…

በተለይ በመጀመሪያ የተጠቀሱት ስንኞች እጅግ የሰመሩ የዜማን ረቂቅ ውበት፤ የሙዚቃን አለማቀፋዊ ቋንቋነት ገጣሚው ያመላከተባቸው ውብ ገለጻዎች ናቸው።

ገጣሚ የቋጠረውን፤ የታዘበውን የተደመመበትን ፍሬ ነገር በስንኝ ቀምሮ ሲወልድ የሚያስተላልፈው ቁምነገር ተደማጭ ይሆንለት ዘንድ፤ የተለያዩ ዘይቤዎችን ይጠቀማል። ለዋሽንት ውዳሴ የተሰደሬት ስንኞች በአነጻጻሪ ዘይቤ ተኩለው ጎልተውና ደምቀው እንደሚከተለው ይነበባሉ።

ክንድ አይሞሌው ዋሽንት - ቀጭኑ ረቂቁ

ትንፋሽ ይለግሳል - ባለትንፋሽ ስንቁ

እንደናት አልቅሶ - እንደ ጅረት ፈሶ

ሰተት ብሎ ገብቶ - እንዳዲስ ፍቅረኛ

ልብን ያማልላል አቅፎት እየተኛ…

በነዚህ ስንኞች ውስጥ የዋሽንት ልብ ሰራቂ ዜማ ቁልጭ ባለ ሁኔታ ተገልጾአል። በተጠቃሎ “እሱን አኑሩልኝ” ዜማን በዜማ የሚያወድስ ግጥም ነው።

ሌላው በመድብሉ ውስጥ የተካተተ ፍርሃት የተሰኘ ፖስተራዊ ግጥም ነው። ገጣሚው ሰበበ ድርሰቱን እንደሚያወጋን ከሆነ የሁለት ሁነቶች ግጭትና በግጭቱ ውስጥ ያለ አንድነት ነው፤ ይህንን ግጥም የወለደው። ከጦር ሜዳ ሸሽቶ ወደ እናቱ ቤት የሚሄድ አንድ ዋቶአደር እና በመስኮት አሻግረው የሚመለከቱ የፊሩ አዛውንት። ታዲያ አበራ እነዚህን ሁነቶች መነሻ አድርጎ የቋጠራቸው ስንኞች በከፊል እንደሚከተለው ይነበባሉ።

ያ መረቡ ልቤ - ረገበ እምቢአለ

አንድ ራሱን ማስገር - ኣቃተው ዋለለ

ፍርሃቴ ስጋቴ - በላዬ ነገሠ

ውስጥ አንጀቴን ምሶ - ቤቴን አጣረሰ

በነዚህ ስንኞች የወንድነት የወኔ የአልበገር ባይነት መጠቀሻ የሆነው ልብ የረገበ መረብ ሆኖ አንድ ራሱን ማስገርተስኖት ሲዋልል እናስተውላለን። ፍርሃት በሰብእና ላይ ነግሶ ቤትን ሲያጣርስ እንታዘባለን። ቤት በዚህ አውደ ንባብ CONTEXT ተምሳሌትነቱ የአንድ ሰው ግላዊ ህይወት፤ የአንድ ማህበረሰብ ህልውና ከፍም ሲል የአንድ አገር እጣ ፈንታ ሆኖ በጥቂት ስንኞችየተወሳሰቡ ሁነቶች የተጣመሩበትና በረቀቀ ሁኔታ የደመቁበት ግጥም መሆኑን ልብ እንላለን።

ይሄው ግጥም እንደሚከተለው ይቋጫል...

እናንተም እንደኔው - ፍርሃት ካባዣችሁ

ጠመንዣው ዣንጥላው - ውሻው ለምናችሁ?

Elegy በሞት የተለየን ሰው የምንዘክርበት፣ ሥራዎቹን፥ ምግባሮቹን አኗኗሩንና አስተሳሰቡን በማውሳት ያንን ሰው የምናስታውስበት የሥነ ግጥም ዓይነት ነው። “ ናጋቲካ ያጋሼኮ” በተሰኘ ግጥሙ አበራ ለማ የሎሬት ጸጋዬን አቢይ ሥራዎች በመጥቀስ፤ በሥጋ የተለየንን ባለቅኔውን ያናግረዋል፣ ይሞግተዋል፣ ይማጸነዋል። በእርግጥም ብላቴን ጌታ ፀጋዬ ታላቅ ባለቅኔ ነውና ሌሎችም በርካታ የጥበብ ሰዎችም ስንኝ ቋጥረውለታል። ወደ አበራ ለማ ከመግባታችን በፊት የደብረ መላእክቱ ባለቅኔ ቦጋለ ዳኘ “ጠብታ” በተሰኘ ርእስ በታተመ የግጥም መድበል መጽሃፍ ውስጥ፤ “ማስታወሻ ለብላቴን ጌታ ሎሬት” በሚል ርእስ ባካተቱት ግጥም የቋጠሩትን ስንኝ እነሆ...

ጸጋዬ ወለልቱ ያ ኢልመ ቀዌሳ

ሜ ወለሎ ቡሲ አኩመ ከሌሳ

ማሎ ሀረ ቡሊ ማልቱ ሲጀርጀርሳ

ቦዴ ዴሙ ወያ ኤኙ ሲአምቢሳ?

አፋን ኦሮሞን ለማያውቁ ግጥሙ በተዛማጅ ትርጓሜ ሲቀኝ ይህን አንድምታ ይዟል።

ጸጋዬ ወልደ ቀዌሳ አንተ ባለቅኔ

እስቲ እንደ ትናንቱ ዝረፍልን ቅኔ

ዛሬን እደር እንጂ ምን ያስቸኩልሃል

ኋላ መሄድ መልካም፥ ማንስ ያስቀርሃል?

እንደማለት ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ አበራ ለማም ሎሬት ጸጋዬ በተወለደበት አካባቢ የሚነገረውን ቋንቋ ኦሮሚፋን ተጠቅሞ ነው ለብላቴን ጌታ ያሚሸውን ሙሾ ርእስ የሰየመው። በኦሮምኛ “ናጋቲካ ያጋሼኮ” በአማርኛ “ደህና ሁንልኝ ጋሽዬ” እያለ።

ታዲያ በዚህ ELEGY ግጥም እሱም ጋሽዬ ያለውን መንገደኛ ባለቅኔ ሥራዎች በማንሳት “ምነው ቸኮልክ?” ይለዋል አበራ፤ የሃዘን፥ የመለማመጥ፥ የመቆጨትና የመማጸን ቅላጼ በዋጠው አንደበቱ።

ኧረ ሞረሽ በሉ - ኧረ በልግንጥሩ

የከርሞ ሰው ጠፋ - እናት አለም ጠኑ

መች እንዲህ ነበረ - ውላችን ቃላችን

ሸልማት ሆነ እንዴ - ላንተ መጮሃችን?

ሸልማት ሆነ እንዴ - ከል መልበሳችን?

ሸልማት ሆነ እንዴ - ቱቢት ስፊታችን

የቀለሙ ቀንዲል - ፈሰህ ማንባታችን?

በተለይም ብላቴን ጌታ ሎሬት ጸጋዬ ለአገሩ ለወገኑ ያለው ፍቅር የተገለጸባቸው ስንኞች እጅግ በጣም ገላጭና ባለቅኔውን በእርግጥም እንድናስታውሰው የሚያደርጉ ሃያል ተግታዎች ናቸው።

ሁሉም እኩል ለሱ - ኦሮሞው አማራ

ትግሬና ሻንቂላ - ሲዳሞ ጊሚራ

አኝዋኩ ወይጦው - ቅማንቱ አፋሩ

ሁሉም ለብላቴን - ያንድ እናት ልጆች

ለሱም ወንድሞቹ -ያውም መንትዮች

.....

ይህ ግጥም የተነበበበት ቅላጼ ከግጥሙ ንባብ ጋር ተያይዞ የቀረበው ምስልና ሙዚቃ ተደራሲን ወደ ጠለቀ ሃዘን የሚከት፣ የቁዘሜውን የመለየቱን ድባብ የሚፈጥር፣ ድንቅ ቅንጅት መሆኑም ሌላው ጠንካራ ጎኑ ነው።

የዚህ የድምጽ፥ የምስል ወ የቅኔቅንጅትና ቁርኝት ከተነሳ EMERSON ን ልጥቀስ። ሰውዬው THE EXPERIENCE OF EACH NEW AGE REQUIRES A NEW CONFESSIOSN, AND THE WORLD SEEMS ALWAYS WAITING FOR ITS POET ነበር ያለው። ታዲያ ቀደም ሲል ቀለም ተበጥብጦ፣ ብራና ተለስልሶ ይከተብ የነበረውን ቅኔ ፤ ግጥም እነሆ የዘመኑን ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ጋዜጠኛ

ክብረት መኮንን በዲቪዲው የተካተቱትን ግጥሞች በምስል ወ ድምጽ አቀናጅቶ ማቅረቡ የሥነግጥም ባለውለታ አያሰኘውምን?

አሁንም የዚህ የምስልና ድምጽ ቅንጅት ነገር ከተነሳ፤ ለአብዛኞቹ ግጥሞች ማጀቢያነት የቀረቡት ምስሎች እጅግ ተገቢ APPROPRIATE እና ማራኪ መሆናቸውን ሳልገልጽ አላልፍም። የግጥሙን መልእክት እና አጠቃላይ ድምጸት በማጉላት ተጨማሪ ማግባቢያዎችም ሆነዋል። ግጥም አይገባኝም በሚል ተለምዷዊ አስተሳሰብ ከቅኔ ማእድ የራቀውን ተደራሲ ወደ ግጥሙ ገበታ የሚመልሱ መሳቢያዎችም ይመስሉኛል።

የመድብሉ መጠሪያ የሆነውና ሌላው አቢይ ግጥም “እውነትም እኛ ልዩ ነን” የተሰኘው ነው። ግጥም ካለው የቁጥብነት ባህሪ አኳያ የግጥም ርእሶች እጥር ምጥን ቢሉ በአንድቃል ቢቋጠሩ ይመረጣል። አንዳንዴ ግን ገጣምያን ሆን ብለው ለመልእክታቸው ማስተላለፊያ። ለጭብጣቸው ማጉሊያ ይሆናቸው ዘንድ እንዲህ አይነቱን ሃረጋዊ ርእስም ያወጣሉ። እውነትም እኛ ልዩ ነን በእርግጥም ቀልብን የሚይዝ የማንበብ ወይም የመደረስ ጉጉትን የሚያጭር ርእስ ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጵያዊ አይነት ኩሩ ህዝብ እውነትም እኛ ልዩነን የሚል መፈክር ሲያጋጥመው የለመደውን ለማንበብ መቋመጡ እሙን ነው።

በታሪክ ለ 27 ጊዜያት በወራሪዎች ተደፍረን ጠላትን አይቀጡ ቅጣት ቀጥተን አሳፍረን የመለስን ብቸኛ አፍሪካውያን እውነትም እኛ ልዩ ነን። አሁን በሥልጣኔ የቀደሙ ሕዝቦች በዋሻና በገደል እርቃናቸውን እየኖሩ፣ ፀሐይና ጨረቃን በሚያመልኩበት ወቅት፣ ህንጻ ቤተ ክርስቲያን ገንብተን እግዚአብሄርን ስናመልክ የኖርን ሃይማኖተኛ ህዝቦች እውነትም እኛ ልዩ ነን። ከዘመናት በፊት የአክሱምን ሃውልት አንጸን ለዘመናዊ ህንጻ ግንባታ ፈር ቀዳጅ የሆን የቀደምት ሥልጣኔ ባለቤቶች እውነትም እኛ ልዩ ነን። እንግዳ ተቀባይ ትሁትና... ወ ዘተርፈ...እውነትም እኛ ልዩ ነን።

እንዲያውም የእንግዳ ተቀባይነታችንን ነገር ታላቁ ባለቅኔ መንግስቱ ለማ “ትዝታ”* በሚል ርእስ በጻፉት ግጥም በሚከተለው አንጓ ገልጠውታል

.....

በቅጽበት ሆንኩና “የግዜር መንገደኛ”

“ጤና ይስጥልኝ ቤቶች” ጥቁር እንግዳቸው መጽደቂያቸው ነኛ!

“ግባ ቤት ለንግዳ” አለኝ ባለቤቱ

ሙቅ ውሃ አቀረበች በቆሬ ሚስቲቱ

ደስ ደስ እያላት ተምበርክካ እፊቴ

እግሬን አጠበችው “አትግደርደሩ እቴ!”

ላንቃዬም ባረከው ያን የጎጃም ጠላ

ገበታ ቀረበ የሆዴ ቋት መላ

.....

እያለ ይቀጥላል። የሃበሻን ጀግንነት፤ አትንኩኝ ባይነት፤ ታጋሽነትና ሃይማኖተኝነት በተመለከተም ብዙዎች ስንኝ ቋጥረዋል። በተለይም ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ “ሃበሾች ይኑሩ” በሚል ርእስ በሳተመው መድብል፤ በዚሁ ርእስ ያቀረበው ግጥም እውነትም እኛ ልዩ ነን የሚያሰኝ ነው።

...

ይኑር ሃበሻዬ

በሰው አገር ምድር በሰዉ ሰማይ

ሁሉን ገለማማጭ “ተዉ አትንኩኝ!” ባይ

“አገር አለኝ እኮ” ብሎ እየፎከረ

ሲሻው አገሬውን እያሸማቀቀ

ካልነኩት ሳይነካ ሲሻው እየቀበጠ

...

ተጨማሪ ስንኞች ልመርቅ ይሆን?

...

ይኑር ሃበሻዬ የድንበር መደፈር የሃገሩን መወረር

ወሬውን ሲሰማ

ለመሰለው አገር አርማና ባንዲራ

ላፈቀረው ታሪክ በክብሩ ሊኮራ

ያለውን ነጻነት አላስነካም ማለት

እያንዳንዱ ራሱን ለክብሩ ሊሰዋ

ለታጠቀ ጠላት አልገብርም ብሎ ሲቀላ ሲቀላ

(የቤት መምቻዋ ሲቀላ “ቀ” የማጥበቂያ ነጥብ አናቷ ላይ ነበራት)

ወደ አበራ ስንመለስ ታዲያ “እውነትም እኛ ልዩ ነን” የለመድነውን ዓይነት ልዩነት የሚያስደምጠን አይመስለኝም።

ገጣሚው በእጅጉ የታዘበንና የተቆጣን ይመስላል። “ዘበት እልፊቱ” በተሰኘ የግጥም መድብሉ ሌላው ወለልቱ ሰሎሞን ዴሬሳ “ከቡር ኢትዮጵያውያን” በሚል ርእስ እንደጣፋት ወለሎ...

“በኢትዮጵያ ባልነ መታየቱ

ሳይሆን ቂንጥር ማስቆረጡ

ህጻኗን ልጅ እንደ ቆዳ መስፋቱ

መባለጉ አፍ ሞልቶ ‘ ቂንጥርን መጥራቱ”

...

እንደጣፋት ወለሎ፤ የአበራ ለማ ብእርም እውነትም እኛ ልዩ ነንን ሲከትብ የተቆጣ ያመረረ ይመስላል።

ላለመስማማት ተዋደን

ላለመዋደድ ተስማምተን

ላለመኗኗር ተቧድነን

ላለመፋቀር ተቃቅፈን

ላለመጋባት ተጫጭተን

ይሄው ዞረን ዞረን እዚያው ነን!

ላለመስማማት መዋደድ፤ ላለመኗኗር መቧደን፤ ላለመፋቀር መተቃቀፍና ላለመጋባት መተጫጨት በአያዎ PARADOX ዘይቤ የተሰናኙ የግጥሙን አጠቃላይ መልእክት የቋጠሩ ምርጥ ስንኞች ናቸው።

....

አጀብ ዘመናችንን ቸብችበን

በኪሳራችን ቶጅረን

የመጠላለፍ ጽዋችንን

ተራበተራ ጨልጠን

ይሄው ሃቻምናናምና ተነበርንበት

እዚያው ዞረን ዞረን ግጥም አልንበት

...

ይህ እንግዲህ የጠነከረ ሂስ ፤የመረረ ግሳጼ፤ ያልተድበሰበሰ ተቃውሞ ነው። ሃምሌ 23 ቀን 2 ሺ ዓ.ም. በዳግም አርትኦት የተጻፈው እውነትም እኛ ሁለንተናዊ ጭብጥ UINVERSAL THEME ይዞ የተነሳ፤ በትንሽ ቀለበት ሲስተዋል በአንድ ንዑስ ቤተሰብ፤ የጓደኝነት ማህበር፤ የሙያ ክበብ ወዘተ ውስጥ ሊከናወን የሚችልን ተገቢ ያልሆነ የመጠላለፍ አባዜ ከፍም ሲል በአንድ ማህበረሰብ ወይም ሃገር ውስጥ የሚታዘቡትን ዓይነት የማን አለብኝነትና የእኔ ብቻ ልግነን ባይነት ብልግና የሚነቅስ፤ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ላይ የተሰነዘረ ተግሳጽ ነው። (የሚሰማ ቢኖር እንዲሉ)

ታዲያ ገጣሚው ትዝብቱን የሚያጋራን እያዋዛም ነው። እየመጸተም ...

እንግዲህ ማን አለ እንደኛ

ዞሮ ዞሮ ተነበረበት የተኛ

ማተብ ጠባቂ ሃቀኛ

ብርቅም አይዶለን እኛ?

ስነግጥምን ከሌሎች የስነ ጽሁፍ ዘሮች የሚለየው ሌላው ተጠቃሽ እሴት ለስሜት ያለው ቅርብነት ነው። እንደ ተደራሲው የንባብ ደረጃና የመገንዘብ ትባት መርቀቁና መድመቁ ነው። ከአንባቢው የህይወት ልምድና አስተሳሰብ ጋር መዛመዱ ነው። በተለይም ዜማዊነቱ የቃላቱ ውበት የመልእክቱ ልብን ሰርስሮ የመግባት ሃይልና አይረሴነቱ ግጥምን ተወዳጅ ያደርገዋል። ተደራሲም እንደ መነካቱ መኮርኮሩ እና መመሰጡ መጠን የተወሰኑ ግጥሞችን በቃሉ አጥንቶ የማነብነብ ታጋት ይስተዋልበታል። የፋርስ ሰዎች

/ኢራናውያን/ የዑማር ካያምን ስም ላነሳባቸው ሰው አንድ ሁለት ሩባይ ሳይወርዱለት አይለቁትም።
/የፋርሱ ቋንቋ ቢገባውም ባይገባውም/

TRANSLATION BY Edward Fitzgerald

Awake! For morning in the bowl of night

Has flung the stone that puts the stars to flight:

And Lo! The hunter of the East has caught

The Sultan‘s turret in a noose of light.

በእድሜ ጠና ያሉ የታላቋ ብሪታንያ ሰዎችም ከሼክስፒር ሶኔቶች* ጥቂት አንጓዎች በቃላቸው መወጣት ደንባቸው ነው።

Sonnet 18

Shall I compare thee to a sommer‘s day?

Thou are more lovely and more temperate:

Rough winds do shake the darling bud of May

And summer‘s lease hath all too short a date:

ሩሲያውያን የፑሽኪንን

I Loved You

I have loved you; even now I may confess,
Some embers of my love their fire retain
but do not let it cause you more distress,
I do not want to sadden you again.

አርመናውያን ደግሞ የቱማንያንን*ቅኔዎች ያነበንባሉ።

In The cottage

The little children wept and wailed;

Heart rending were the tears they shed.

“Mamma, mamma we want our food!

Get up mamma, and give us bread!“

እቅኔ ቤት የከረሙ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም በአጼ በካፋ ላይ የተቀኘችውን ይህቺን ጉባኤ ቃና በቀላሉ ሲወጧት ይስተዋላል

በካፋ ኢትርሳእ ዘተዋነይነ ክልኤነ

እንዘ አንተ አበ አብራም ወ አነ ብእሲተ አብራም

የቅኔው ትርጓሜ በካፋ አንተ የአብርሃም አባት (ታራ) እኔ ደግሞ የአብርሃም ሚስት (ሳራ) ሆኜ የተጫወትነውን እንዳትረሳ የሚል ነው። ታሪኩም አጼ በካፋ ከቅኔ ቤት ጓደኞቸው ጋር በልጅነት ሲጸዳዱ የተጫወቱትን የሚያስታውስ ነው።

/ልብ በሉ የዚህ ባለቅኔ ስም አይታወቅም። ቅኔው ግን ከነገስታት ውሎ ጋር ተቆራኝቷልና እነሆ ዘመን ተሻግሮ ይታወሳል።/

ብዙዎቻችን የስነጽሁፍ ተማሪዎች በቃላችን አጥንተን የምናነበንባት ተጠቃሽ ግጥም ደግሞ የመንግስቱ ለማ በጠራ ጨረቃ* ናት

በጠራ ጨረቃ በኩለ ሌሊት

አይኖቿ እያበሩ እንደከዋክብት

ሳማት ሳማት አሉት እቀፍ እቀፋት

አላወላወለም ወጣቱ ታዘዘ...

ታዲያ በዚሁ አካሄድ የአበራ ለማን ግጥም በቃሉ አጥንቶ ሲያነበንብ በዲቪዲው ላይ የተስተዋለው ወጣት ደረጀ መኮንን ከሰላሳ አመታት በፊት የታተመው መቆያ መጽሃፍ ውስጥ ያነበበው ስንብት በልጅነት አእምሮው ታትሞ መክረሙን ይናገራል። እኔም በወጣቱ አንደበት ጥቂት ስንኞች ልከተብና ልሰናበት።

ምስቅልቅሉን ኑሮ ህይወቱን ቢጠላ

ባጭር ገመድ ጠራው እድሜውን ሊበላ

ላፍታ ጸጥ አለና ውስጡን አዳመጠ

ከነጣው መራቆት መሄዱን መረጠ...

*የመንግስቱ ለማን “ትዝታ” እና “በጠራ ጨረቃ” ሙሉውን ለመደረስ የግጥም ጎባኤን ፈልጎ ማንበብ፤ የሼክስፒርን ሶኔት ሙሉውን ለማንበብ የሰውዬውን ሶኔቶች ሙሉውን እቤተመጻህፍት መፈለግ፤ እንዲሁ የቱማንያንን ስራዎች የፑሽኪንንም ኢንተርኔት በመጎርጎር ጭምር ማንበብ ይቻላል!!! ሰላም ለኩልክሙ ።